በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ አሪዞናእና ቅድስት ማርያም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሎስ አንጀለስ ሐገረ ስብከት ጽ/ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahdo Church
Diocese of Northern California, Nevada
Arizona and St. Mary's of Ethiopian Orthodox
Tewahdo Church in Los Angeles Main Office

ቀን: መጋ 04 2012
Date: Mar13 2020
ሰካሀጽ/0704/12
Ref.No.031620

<u>በሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ለምትገኙ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ</u>

<u>ጉዳዩ፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለተከሰተው የኮሮና ቫይረስ አስመልክቶ ይሆናል፤</u>

በቅድሚያ የዓለማት ፈጣሪ የሁላችን አምላክ የልኡል እግዚአብሔር ሰላም በያላችሁበት ይብዛላችሁ እያልን ወቅቱን በማስመልከት የአብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮች እና ምእመናን አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንድታደርጉ እና በጸሎት እንድትተጉ በብጹእ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቴዎፍሎስ የሚመራው የሐገረ ስብከታችን ጽ/ቤት የሚከተለውን መልእክት ያስተላልፋል።

1. እንደሚታወቀው በሽታው በዓለም የጤና ድርጅት ታውቆ ከቀላል እስከ ከባድ የመተንፈሻ አካል ሕመም የሚያስከትል እንደሆነ መግለጫ ስለተሰጠበት አብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊው አገልግሎታችሁ አስፈላጊውን የመከላከል እና የዝግጁነት ሥራ እንድትወስዱ እና ጉዳዩን በማስመልከት የጀመራችሁት ሥራም ካለ አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ በአክብሮት እናሳስባለን።
2. በተጨማሪም የበሽታውን መተላለፊያ መንገድ መንስኤ እና የመከላከያ እርምጃ አስመልክቶ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት ወይም መንግስት የሚያስተላልፈውን መረጃ አብያተ ክርስቲያናት በትኩረት እየተከታተላችሁ ለምእመናን እንድታሳውቁ እና በጸሎት እንድትተጉ በአክብሮት እናሳስባለን
3. በሽታውን ለመከላከል እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ ቁልፍ የበጎ አድራጎት እና ነጻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግስት የጤና ድርጅቶች ጋር በሀገር አቀፍ እንዲሁም በስቴት ደረጃ አቅም በፈቀደ መልኩ አብያተ ክርስቲያናት ትብብር እንድታደርጉ በአክብሮት እናሳስባለን።
4. የበሽታው ስርጭት ቁጥር በጉዞ አማካይነት እና የሕዝብ ስፋት ስብስብ ባለበት ሁሉ እየጨመረ ስለሚገኝ አብያተ ክርስቲያናት የመንፈሳዊ ጉዞ መርሐግብር እና የታላላቅ ጉባኤ መርሐግብር እቅዶቻችሁን ላልተወሰነ ጊዜ እንድታዘገዩ በአክብሮት እናሳስባለን።
5. በመጨረሻም ከምንኖርበት ሀገረ መንግስት እና የስቴት መንግስት ስለበሽታው የሚተላለፈውን መመሪያ በመከታተል በያላችሁበት ተፈጻሚ እንድታደርጉ በአክብሮት እያሳሰብን የተወደዳችሁ ካሕናት እና ምእመናን ይህን ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ለመከላከል እና ለማስወገድ አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ እያደረጋችሁ በጸሎት እና ምሕላ እንድትተጉ በአክብሮት እናሳስባለን። እግዚአብሔር አምላካችን ዓለማችንን በምሕረቱ ይጎብኘን። የቅዱሳኑ ጸሎት የድንግል ማርያም ምልጃ ይጠብቀን።

''ከመንፈሳዊ የአክብሮት ሰላምታ ጋር''

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
- ለሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ስቴት ቤተ ክሕነት
- ለሚመለከተው ሁሉ

Melakeselam Marye Kahisay
General Manager of Northern California,
Nevada and Arizona Dioceses